የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፯ ቀን ፳፻፲

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No. 37
ADDIS ABABA 26th February, 2018

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፬/፳፻፲ ዓ.ም
ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማስፈፀሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ………………ገጽ ፲ሺ፫፻፴፫

## Content

Regulation No. 424./2018
State of Emergency Proclamation issued to defend the Constitution and the Constitutional order from threat proclamation Implementation of Council of Ministers Regulation…Page 10333

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፬/፳፻፲

### ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመካለከከል የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፪/፳፻፲ ማስፈፀሚያ ደንብ

ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ስርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል በወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፪/፳፻፲ አንቀጽ ፲፯(፩) መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እንደሚያወጣ በመደንገጉ፣

ይህን ተከትሎ የአስቸኳይ ጊዜ ኮማንድ ፖስት አዋጁን ለማስፈፀም በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሚከተላቸውን ዝርዝር አቅጣጫዎች በዚህ ደንብ መደንገግ በማስፈለጉ፣

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 424/2018

### A STATE OF EMRGENCY PROCLAMATION ISSUED TO DEFEND THE CONSTITUTION AND THE CONSTITUTIONAL ORDER FROM THREAT PROCLAMATION No.2/2018 IMPLEMENTATION OF REGULATION

**WHEREAS,** it has been stipulates under the sate of Emergency Proclamation issued to defend the Constitution and the Constitutional order from threat proclamation No. 2/2018 article 17(1) that the Council of Ministers shall issue Regulation;

**WHEREAS,** following this, it has become necessary to decree under this Regulation detailed directions that the State of Emergency Command Post follows based on the power given to it to implement the proclamation;

**NOW, THEREFORE**, the Council of Ministers hereby issues the following Regulation.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "State of emergency Proclamation issued to defend the

አዋጅ ማስፈፀሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፬/፪ሺ፲"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

፩/ "አዋጅ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሕገ መንግስቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፪/፪ሺ፲ ማለት ነው።

፪/ "የአስቸኳይ ጊዜ ኮማንድ ፖስት" ማለት በአዋጁ አንቀጽ (፮) የተቋቋመው ኮማንድ ፖስት ማለት ነው።

፫/ "ተሀድሶ" ማለት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ለማስፈፀም በሚወሰዱ እርምጃዎች የሚያዙ ሰዎችን ተገቢውን ትምህርትና ስልጠና በመስጠት ወደ ህብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ ማድረግ ማለት ነው።

፬/ በአዋጁ ላይ የተሰጡ ሌሎች ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**፫. <u>የአስቸኳይ ጊዜ ኮማንድ ፖስት አዋጁን ለማስፈፀም የሚከተላቸው አቅጣጫዎች</u>**

በአዋጁ አንቀጽ (፬) ላይ የተዘረዘሩን ተግባራት ለመፈፀም የአስቸኳይ ጊዜ ኮማንድ ፖስት፡-

፩/ በሀገሪቱ በአጠቃላይ ወይም በተወሰነ ቦታ እንዳይፈፀሙ የተከለከሉ ተግባራትን ይለያል፤

፪/ የተከለከሉ ተግባራት ተፈፅመው ሲገኙ ስለሚወሰዱ የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎች ይወስናል፤

፫/ መረጃ የመስጠትና የማስታወቅ ግዴታን እና መረጃን የሰጠ ሰው ጥበቃ ስለሚያገኝበት ሁኔታ ይወስናል፤

፬/ አጥፊዎች ለህግ ስለሚቀርቡበትና ተሀድሶ ተሰጥቷቸው ስለሚለቀቁበት ሁኔታ ይወስናል፤

Constitution and the constitutional order from threat proclamation Implementation of Council of Ministers Regulation No. 424/2018".

**2. <u>Definitions</u>**

1/ "Proclamation" means State of Emergency Proclamation issued to defend the Constitution and the Constitutional order from threat proclamation No. 2/2018.

2/ "State of Emergency Command Post" means Command Post established under article (6) of the proclamation.

3/ "Rehabilitation" means integrating to the society those individuals arrested based on measures taken to implement the State of Emergency Proclamation by providing relevant education and training.

4/ Definitions provided under the Proclamation shall also be applicable to this Regulation.

**3. <u>Directions to be followed by the State of Emergency Command Post to implement the Proclamation</u>**

The State of Emergency Command Post to implement activities listed under article (4) of the Proclamation shall;

1/ Identify acts which are prohibited at nationwide or limited place;

2/ Determine emergency measures to be taken when prohibited acts are committed;

3/ Determine conditions of the duty to inform and give information and the protection of persons who provide information;

4/ Determine conditions under which perpetrators are released after receiving rehabilitation and may be brought to justice;

፭/ በተከለከሉ ቦታዎች አደጋ የሚያደርሱ ግለሰቦች ወይም ቡድኖችን እንዲሁም ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ከጉዳት ለመታደግ ሲባል በተወሰነ ቦታ እንዲቆዩ ወይም እንዲወጡ የሚደረግበትን አቅጣጫ ይወስናል፤

፮/ በአጠቃላይ የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ ሲባል የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ በዝርዝር በማገናዘብ አስፈላጊውን የጥንቃቄና የመከላከል እርምጃ ይወስዳል፤

፯/ ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለማስከበር፣ ከአደጋ ለመጠበቅ፣ የህዝብና የዜጎች ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ ሁሉንም እርምጃዎች ይወስዳል፤

፰/የህግ አስከባሪ አካላት ስምሪት እና ቅንጅት የህብረተሰቡን ተሳትፎ በሚያረጋግጥ መንገድ ሥራዎችን ይመራል፡፡

፬/ <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

የአስቸኳይ ጊዜ ኮማንድ ፖስት አዋጁን እና አዋጁን ተከትሎ የወጣውን ይህን ደንብ ለማስፈፀም ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣል።

፭. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ አዋጁ በስራ ላይ ባለበት ጊዜ ተፈፃሚ ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት ፱ ቀን ፪ሺ፲ ዓ/ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይሚኒስትር**

5/ Determine the direction under which persons or groups or sections of the society vulnerable to danger stay in a certain place or evacuate from a given place to protect them from danger;

6/ Take necessary precautionary and preventive measures to protect the peace and security of the public by considering in detail the practical situations;

7/ take all necessary measures to d To defend the Constitution and the constitutional order from threat and to maintain public and citizens peace and security;

8/ Lead activities of deployment and coordination of law enforcement organs by ensuring public participation.

**4. <u>Power to Issue Directives</u>**

The State of Emergency Command Post shall issue detailed implementation directives to implement the Proclamation and the Regulation.

**5. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall remain in force from its adoption until the time the proclamation is in effect.

**Done at Addis Ababa, this16th day of February ,2018.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**